ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ GLOBAL BANK ETHIOPIA
OUR SHARED SUCCESS

# ለግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ አ.ማ. ባለአክሲዮኖች በሙሉ

## የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ መስፈርት ለማሳወቅ የወጣ ማስታወቂያ

ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ አ.ማ. ታህሳስ 19 ቀን 2017 ዓ.ም ፒያሳ በሚገኘው የዓድዋ ድል መታሰቢያ የስብሰባ አዳራሽ በሚያካሂደው 11ኛ የባለአክሲዮኖች መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ላይ የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ምርጫን ያካሂዳል፡፡

በመሆኑም በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ ቁጥር SBB/91/2024 አንቀጽ 9(3) መሠረት የጥቆማና ምርጫ መስፈርት ምርጫው ከሚካሄድበት ቀን አንድ ወር በፊት ለባለአክሲዮኖች መገለጽ እንዳለበት በሚደነግገው አግባብ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ዕጩዎችን በስብሰባው ዕለት መጠቆምና መምረጥ እንድትችሉ ለመላው የባንካችን ባለአክሲዮኖች ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

### የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆኖ ለመመረጥ ዕጩዎች ማሟላት ያለባቸው መስፈርቶች

1. የቦርድ አባላት ምርጫ ከሚደረግበት ዕለት ሁለት ዓመታት በፊት የባንኩ ባለአክሲዮን የሆነ፣
2. የቦርድ አባል ሆኖ ለመሥራት ሙሉ ፍቃደኛ የሆነና ኃላፊነቱን በአግባቡ ለመወጣት በቂ ጊዜ ያለው፣
3. ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው ወይም ተመጣጣኝ የትምህርት ደረጃ እውቅና ካለው ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ያገኘ፣
4. ከባንክ ሥራ ጋር ተዛማጅነት ባላቸው መስኮች ማለትም በባንኪንግ፣ በፋይናንስ፣ በሪስክ ማኔጅመንት፣ በአካውንቲንግ፣ በማኔጅመንት፣ በኢኮኖሚክስ፣ በሕግ፣ በቢዝነስ አድሚኒስትሬሽን፣ በኦዲት፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ በኢንቨስትመንት ማኔጅመንት፣ በማህበራዊና አካባቢ ጥበቃ፣ በዘላቂነት (Sustainability) እና በተዛማጅ የሙያ ዘርፍ ቢያንስ 7 (ሰባት) ዓመት የሥራ ልምድ ያለው፣
5. ከዳይሬክተር የሚፈለጉ ግዴታዎችን ለመወጣት ከጥቅም ግጭቶች ነጻና ገለልተኛ በመሆን ከሌሎች የቦርድ አባላት ጋር በአብሮነት መሥራት የሚችል እና ጥሩ ተግባቦት ያለው፣
6. ዕድሜው 30 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣
7. ሃቀኛ፣ ታማኝ እና መልካም ዝና ያለው፤ በተለይም በማጭበርበር፣ እምነት በማጉደል፣ ትክክለኛ ያልሆነ የሂሳብ መግለጫ በማቅረብና በመሳሰሉት ተከሶ በፍ/ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ተሰጥቶበት የማያውቅ፣
8. በሌላ የፋይናንስ ተቋም የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ወይም ዋና ሥራ አስፈጻሚ ወይም ሠራተኛ ያልሆነ፤
9. በራሱ ወይም በሚመራው ወይም ዳይሬክተር በሆነበት ድርጅት ላይ የመክሰር ክስ ያልቀረበበት ወይም የኪሳራ ውሳኔ ያልተሰጠበት፣
10. ከአራት በላይ በሆኑ ተቋማት ውስጥ በቦርድ ዳይሬክተርነት እየሰራ ያልሆነ፣
11. በኪሳራ ምክንያት ንብረቱ ለዕዳ ማቻቻያነት ያልዋለበት፣
12. የባንክ ብድር ባለመክፈሉ ምክንያት ንብረቱ በሐራጅ ያልተሸጠ፣ ተከሶ ያልተፈረደበት ወይም እሱ የሚመራው ወይም ዳይሬክተር የሆነበት ድርጅት ከገንዘብ ተቋማት የተበደረውን ገንዘብ ባለመክፈሉ ብድሩ ወደ ጤናማ ያልሆነ የብድር ደረጃ ያልዞረበት/ያልገባበት፣
13. በቂ ስንቅ/ገንዘብ ሳይኖር ቼክ ሰጥቶ ሂሳቡ ያልተዘጋበት፣
14. ግብር ባለመክፈል ተከሶ ጥፋተኛ ያልተባለ፣
15. በስብሰባው ዕለት የሚመረጠው ጊዜያዊ የቦርድ አስመራጭ ኮሚቴ አባል ያልሆነ፣
16. በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የወጡ መመሪያዎች ላይ የተገለጹት ሌሎች መመዘኛዎችን የሚያሟላ መሆን አለበት፡፡

### ማሳሰቢያ

- በተሻሻለው የባንኩ መመስረቻ ጽሑፍ መሠረት በአጠቃላይ የሚመረጡት የዳይሬክተሮች ቦርድ አባላት ቁጥር 9 ሲሆን፤ የምርጫው አፈጻጸምን በተመለከተ፣
  - 1/3ኛ የቦርድ አባላት ተፅዕኖ ፈጣሪ ባልሆኑ ባለአክሲዮኖች ተጠቁመው በእነዚሁ ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ፣
  - 1/3ኛ የቦርድ አባላት በሁሉም ባለአክሲዮኖች ተጠቁመው በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ፣
  - እንዲሁም 1/3ኛ የቦርድ አባላት በነባር ቦርድ ተጠቁመው በሁሉም ባለአክሲዮኖች የሚመረጡ ገለልተኛ ዳይሬክተሮችን (Independent Directors) በመምረጥ የሚከናወን ይሆናል፡፡
- የገለልተኛ ቦርድ አባላት (Independent Directors) ዕጩዎች ጥቆማን ሳይጨምር የሁሉም ቦርድ አባላት ጥቆማና ምርጫ የሚካሄደው በመደበኛ ጠቅላላ ጉባኤው ዕለት ነው፡፡
- በዕለቱ በመጀመሪያ የምርጫ ፖሊሲና ደንብ ከጸደቀ በኋላ አስመራጭ ኮሚቴ ይመረጣል፡፡
- ባለአክሲዮኖች ጥቆማ ሲሰጡ ስለዕጩው የትምህርት ብቃትና የሥራ ልምድ፤ እንዲሁም የጠቋሚውን ማንነትና ያለውን የአክሲዮን መጠን በተመለከተ አጭር ማብራሪያ መስጠት አለባቸው፡፡
- አንድ ባለአክሲዮን ራሱን በእጩነት መጠቆም ይችላል፡፡
- አሁን ያሉ ዳይሬክተሮች ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት በድጋሚ ሊመረጡ ይችላሉ፡፡
- ከአጠቃላይ የቦርድ አባላት ውስጥ ቢያንስ ሁለት ሴቶች በቦርድ አባልነት መመረጥ አለባቸው፡፡
- ቦርዱ በቂ የፆታ፣ የትምህርት ዝግጅትና የሥራ ልምድ ስብጥር ያለው ሊሆን ይገባል፡፡
- ሁለት የባንኩ ሠራተኞች የዳይሬክተሮች ቦርድ አባል ሆነው ሊመረጡ ይችላሉ፤ ይህ ግን የማህበሩን ፀሐፊ አያካትትም፡፡
- በወንድ ፆታ የተገለፀው ለሴት ፆታም ያገለግላል፡፡

**የማህበሩ ፀሐፊ**

**ግሎባል ባንክ ኢትዮጵያ አ.ማ.**